# ይህ አገር የማን ነው?

በአገርም ሆነ በአካባቢ ደረጃ የምናልፍባቸው አጋጣሚዎች መሰረታዊ ጥያቄ እንድናነሳ የሚጋብዙበት ጊዜ ሞልቷል። ያለመልስ ከማልፋቸው መሰል ጥያቄዎች አንዱ “ይህ አገር የማን ነው” የሚል ነው።ይህን ጥያቄ በዚህ ሰሞን እንዳስታውሰው ያደረገኝ በአገራችን ጉዳይ መነጋገርም ሆነ  መሳተፍ ተስፋ አስቆርጧቸው  ያገኘኃቸው ወጣቶች ናቸው። እውነት ግን ይህ አገር የማን ነው?

ቀላሉ መልስ “የሁላችንም” የሚል ነው መሆንም ያለበት እሱው ነው። አገርን የጋራ የሚያደርጋት ግን መብትና ሐሊዮታዊ አመክንዮ ብቻ አይደለም።ሁለቱን ወደ ተጨባጭ እውነትነት የሚቀይረው ማህበረሰባዊ  አመለካከትና ስርአትን ይጠይቃል። አካባቢያችን ይህ ስሜት እንዲሰማን የሚያደርግ ስለመሆኑ በእርግጠኝነት  መናገር ይከብደኛል።ሁሉም መረጃ ስለሌለኝ። ነገር ግን ጥያቄውን ደጋግሜ እንድጠይቅ የሚያስገድዱኝ ነገሮች መኖራቸው እውነት ነው። ኢትዮጵያ የእኔ ያልሆነች ያህል ወይም “የእነርሱ ብቻ” የሆነች ይመስል ሌላውን ዜጋ በማግለል ለራሳቸው የሰጡትትን የባለቤትነት እውቅና ሰርቲፍኬት በአደባባይ ሊያሳዩን የሚፈልጉ ሰዎች ሞልተዋል። ከነዚህ የሚበዙት ግን በውሸት ሕይወት እንደሚኖሩ እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ እኛም እናውቅላቸዋለን።ለአገርና ለወገን አሳቢዎች ለልማትና ለዲሞክራሲ ተቆርቃሪዎች ለሰላምና ለወንድማማችነት የሚሞቱ መስለው በየመድረኩ የሚዘባርቁ የአለቆቻቸውን የታማኝነት ሰርቲፍኬት ለማግኘት እንደሆነ የማይታወቅባቸው ይመስላቸዋል። ነገር ግን እውነቱን አያመልጡትም፤ አይቀይሩትም እውነት ውሏን አትስትማ።

እነዚህ ዞምቢዎች ናቸው ስለለውጥ  እየሰበኩ የተበላሸውንና ያረጀውን  አመለካከትና አሰራር በተግባር ህያው የሚያደርጉት፡ እነዚህ ፍጥረታት ናቸው። እራሳቸውን ያገር ባለቤትና አሳቢ አድርገው በመሾም ሌላውን ዜጋ ተጠርጣሪ ጠላት አድርገው የሚያስቀምጡት እነዚህ መናፍስት የእነርሱን አንደኛ ደረጃ ባለቤትነት ለማረጋገጥ በየትም ቦታ የትኛውንም መንገድ ይጠቅማሉ በማንም ላይ ስም ያጠፋሉ፤ የሀሰት ማስርጃ ይፈበርካሉ፤ ይዋሻሉ፤ ያስፈራራሉ፤ ይካሰሳሉ፤ ይጮሃሉ፤ ይቀጥፋሉ፤ ያጭበረብራሉ፤ ያወራሉ፤ ይጽፋሉ፤ ያማሉ፤ ይገድላሉ፤ ትዝ አሏችሁ? የእነዚህን ዞምቢዎች ተፈትሮአዊ ባህሪ ካልተረዳንና ተገቢውን ህሊናዊ ተግባራዊ ምላሽ ካልሰጠናቸው ጥፋታቸው ለአገር መትረፉ የተረጋገጠ ነው። እነርሱ አገራችንን በተግባርም ሆነ በንድፈ ሀሳብ የእነርሱ ብቻ የሆነች ባደረጓት መጠን ሌላው ዜጋ ራሱን ከአገሩ ጉዳይ ማግለል ይጀምራል፡ ያገሩን ነገር የራሱ አድርጎ መመልከቱን ይተወዋል ።በመጨረሻም አገሩን እራሷን ይረሳታል፤ ይጠላታል፤ ከአገሩ የዜግነትን ትርጉም ያጣባታል። በገዛ ሀጋሩ መጻተኛ በአድ ሆኖ ይኖራል።

እነርሱ ለገዜው ሀብትና ንብረት ማግበስበሳቸውን በህግም ሆነ በሌላ  መንገድ ባገኙት ስልጣንና ተሰሚነት የአስተሳሰብና የደም ዘመዶቻቸውን መጥቀማቸውን በግለሰብም ሆነ በቡድን በዘላቂነት የበላይ ሆነው የሚኖሩበትን መደላደል ለመፍጠር መሞከራቸውን እንጂ እያስከተሉ ያሉትን አገራዊ ጥፋት ማስተዋል አይችሉም አይፈልጉምም።

ዞምቢዎቹ ሌላውን ዜጋ ለአገሩ የማያስብ ለህዝቡ የማይቆረቆር አድርገው የሚያቀርቡት ኩሳዊ የግልና የቡድን ጥቅማቸውን በፍጥነት ለማግበስበርስ ብቻ አይደለም፤ ህልውናቸው የተማሰረተው እኛን በዚያ አይነት የመገለል ስሜትና እውነታ ውስጥ እንድንኖር በማድረግ ላይ ስለሆንም ጭምር ነው።ሌላው ዜጋ  ስለአገር ማሰብና መቆርቆር የእርሱ እንዳልሆነ ይህን ለማድረግም እንደማይችል ወይም ሌሎች በሀብት በእውቀትና በደም ለአገር ለማሰብ ከእነርሱ የተሻሉ ሰዎች እንዳሉ በማሰብ ከጨዋታው ገለል እንዲልላቸው ይፈልጋሉ።

ዜጎች ስለገራቸው ማሰብን ለዞምቢዎች በሚሰጡበት ማህበረሰብ ውስጥ ዲሞክራሲ የዜጎች መብት ማስከበሪያ ሳይሆን የመጨቆኛ መሳሪያ ይሆናል። ሁሉም አይነት ሙስና የተግባር መመሪያ ይሆናል። ሕግና የሕግ የበላይነት የፍትህ መፈለጊያ መሆኑ ይቀርና ማስፈራሪያና ማጥቂያ ይሆናል።ልማትና ብልጽግና የሁሉም ዜጎች መሻት መብት ተክዶ ጥቂት ብጹአን ብቻ የቆሙለት ጽድቅ ተደርጎ ይቆጠራል።ማህበረሰብ በድህነት በደንቁርናና በአባገነናዊ ስርአት ውስጥ እንዲኖር ራሱን የረገመ ሆኖ ይገኛል።

ዞምቢዎች ሁሉንም የህብረተሰባችንን የሂወት መስክ መቆጣጠርና መምራት ይፈልጋሉ። በዚህ ሂደትም እነርሱ ያገራችን ባለቤቶች እኛ ደግሞ ዝምተኛ ተመልካቾች እንድንሆን ሁሉንም ነገር ያደርጋሉ። ስለሀገራችን አስበን ስንናገር ሊያሸማቅቁን ይሞክራሉ።ስለ ኢትዮጵያችን እጣ ፈንታ በጋራ እንነጋገር ብለን ስንቀመጥ ማሰባችንን ወንጀል አድርገው

ያቀርቡታል።በየትኛውም ጉዳይ ላይ ከእነርሱ ፓርቲ ፤እድር፤ ማህበር፤ እምነት ወዘተ የተለየ ሀሳብ በማቅረባችን እንድናፍርና እንድንፈራ ይጠይቁናል።

የዞምቢዎቹ ህልም ሁሉም ዜጋ ስለሚበላውና ስለሚጠጣው ምን አልባትም ስለልብስና ስለመኖሪያ በማሰብ ብቻ እንዲጠመድ ነው።የእለት ኑሮውን ከማሸነፍ ያለፈ ፍላጎት ያለው ዜጋ እንዳይኖር ምኞታቸው ነው። በወደዱት ቅርጽና መልክ አካባቢያቸውን በነጻነት ለመርዳትና ለማስረዳት ሲሞክሩ ዞምቢዎች አይናቸው ይቀላል።የህልውናቸው መሰረት በሌሎች ዜጎችና ህዝቦች የእርስ በእርስ ጥርጣሬ ላይ የቆመ በመሆኑም የአንዱ ብሄር አባል ስለሌላው በጎ ሲያስብና ሲጨነቅ መመልከት አያስፈልግም ሁል ጊዜም በሳዊ ፍላጎታችን ስቀንና በዚያ ሀሳብ ተጠምደን እንድንኖር ይፈልጋሉ። ስለነጻነትና ስልዲሞክራሲ ስለ እኩልነትና ስለሰላም ወዘት. የምናስብበትና የምንነጋገርበትን እነሱ የማይቆጣጠሩት አጋጣሚ መድረክ ተፈጥሮ ሲመለከቱ ይደነግጣሉ ይረበሻሉ በነጻነት ሀሳብ ከተለዋወጥን እየተጋጨንም ቢሆን ልንቀራረብ ነዋ! በነጻነት ከተቀራረብን ከቁሳዊ ሰቀቀን ትረካ አምልጠን ስለ ነጻነትና እኩልነት ማሰን ልንጀምር ነዋ። በነጻነት መንፈስ መኖር ከጀመርን ሽህወች የሞቱለትና ዞምቢዎቹ የሚነግዱባት ኢትዮጵያ እውነት ልትሆን ነዋ!።

አገርን የማዘመን ህብረተሰብን የማበልጸጉ ነጻነትን ለሁሉም ሰው የማረጋገጡ ሀላፊነትና መብት በየትኛውም ማህበረሰብ እራሳቸውን ለሾሙ ዞምቢዎች ተሰጥቶት አያውቅም። በእኛም ማህበረብ ቢሆን ይህ ሊሆን አይገባም አይችልምም።ይህን ጽሁፍ እንድጫጭር መነሻ የሆኑኝ በዜግነታቸው ስሜታቸው የተነካ ወዳጆቻ ራሳቸውን ለአገር ከማሰብ ስለ ሀገር ከመነጋገርና ከመስራት ወዘተ...ባገለሉ መጠን በዞምቢዎች ዓለም እልልታ እንዲኖር ባይፈቅዱ እመኛለሁ።

ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት የዞምቢወቹም ጭምር። አሁን ግን ፈተናው ዞምቢዎች በማስፈራራት በመወንጀል ስም በማጥፋት ወዘተ."ብዙ ዜጎች ከማህበራሰባዊ ህይወት ማግለል ይችላሉ ወይስ እኛ የአገራችንን የጋራ መሆኗን እናረጋገጥላቸዋለን?" የሚል ነው።

በግሌ ማንም ኢትዮጵያ የእኔም ጭምር መሆኗን እንዲነግረኝ ወይም ይህን እንዲያረጋግጥልኝ አልፈልግም አልፈቅድምም።ይህን የባለቤትነት ድርሻ ማንም አልሰጠኝም ማንም አይነፍገኝም ብዬ አምናለሁ።ይህን መሰሉ አመለካከት ሰላም የሚነሳቸው ሰዎች ቢኖሩ እናታችን ኢትዮጵያ ለሁላችንም እንደምትበቃ እና ለሁላችንም የምትሆን አገር ልናስደርጋት እንደምንችል ከመንገር በቀር የማደርገው ነገር አይኖርም። በፖለቲካዊ፤ በኢኮኖሚው በማህበራዊ ዘርፍ ከመንደር እስከ ቀበሌ ከቤተክርስቲያን እስከ ክልል ቢሮ ከመስጊድ እስከ ፌደራሉ መንግስት ድረስ በየደረጃው "ተገለለን አያገባችሁም ዝም በሉ ከዳቦ ሌላ ሀሳብ አይኑራችሁ አይገባችሁም ወዘተ." የሚባሉ ውድ ወገኖቻ እንዳሉ መገመት እችላለሁ። አባቢዎቻም ይኸው ስሜት ገጥሞአችሁ ይሆናል።

ምንም ቢሆን ግን የባለቤትነት ድርሻችንን የዜግነት መብታችንን አሳልፈን ለመስጠት የተዘጋጀን ሆነን እንዳንገኝ ምኞቴ ነው። ስለ ሀገራችን በማሰብ የምናቀርበው ሀሳብ እና የምናከናውነው ሰላማዊና ህጋዊ ተግባር ምንም ይሁን ማንም ይቀበለው ወይም አይቀበለው አቅማችን እስከ ፈቅደ ድረስ ይህን በማድረግ ካልተጓዝን እኛ ምንድን ነን። የሚግጠውን ሳር ብቻ ከሚፈልግ ወይም ለራሱ ቁሳዊ ሰቀቀ ስል የሌላውን ነጻነት ከመንፈግ የማይመለስ ዞምቢ በምን ተለዬ? ዞምቢዎች ማህበረሰብ ፈጥረው አያውቁም የተፈጠረውን ለማፍረስ ግን የሚቀድማቸው የለም።

አንድ ሀገር የጥቂቶች ትሁን የብዙሀን ለማሳየት እጅግ በርካታ መመዘኛዎችን መደርደር ይቻላል። ይህ ግን ለአንባቢዎቻ ልተወው። ፈረጆቹም እንዲህ ያለ ፈተና ሲገጥማቸው ዝነኛ ለመሆን የበቃ ጥያቄአቸውን ይወረውራሉ **"whose country is it anyway"?**